# እናቸንፋለን/እናሸንፋለን

እነዚህ ቃላቶች፣ በትርጉም ደረጃ ምንም ልዩነት የላቸውም። ከየካቲቱ አብዮት በኋላ ባጠቃቀም ላይ ኢሕአፓ እንቸንፋለን የሚለውን ቃል ሲጠቀም፣ መኢሶን ግን እናሸንፋለን የሚለውን ቃል መርጧል። ሁለቱ ድርጅቶች በፖለቲካቸውና በሚያራምዱት ፖሊሲያቸው ላይ፣ መሰረታዊ በሆኑና በርከት ባሉ  አቋሞች ላይ ልዩነት ነበራቸው። ልዩነታቸውም፣ በፖለቲካ ድርጅት ደረጃ ሳይደራጁ፣ ገና በተማሪ ማኅበር ደረጃ እያሉ ጀምረው የተገለጹና በኋላም አድገው በድርጅት ደረጃ ሁሉ የተገፉ ናቸው።

ደርግ የመንግሥት ስልጣኑን ይዞ፣ ኢሕአፓን በጠላትነት ከፈረጀና፣ ቆየት ብሎም ከመኢሶን ጋር ከተለያየ በኋላ የነዚህን ሁለት ቃላት አጠቃቀም ልዩነቶች እንደ ትልቅ ነጥብ በማምጣት ሁለቱ ድርጅቶች በነዚህ ሁለት ቃላት ልዩነት ብቻ ተጣልተው እንደተዋጉ አድርጎ ለፖለቲካ ፍጆቱ በመጠቀም በስፊው ተጠቀመበት። ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል እንደሚባለውም፣ ዘወር ብለው ጠቅላላ ፖለቲካዊ ሂደቱን ሳያጤኑና ሳይመረምሩ የተወሰኑ የሕብረተሰቡ ክፍሎች እንደ እውነት ተቀበሉት።

በዚህ ብቻ አያበቃም። ደርግ በውርደት ከስልጣኑ ወርዶ፣ ያ ደርግ ያስጀመረው መሰረት የሌለው በቃላት ልዩነት ተዋጉ የሚለው ፕሮፖጋንዳ ከጠፋ ምንም እንኳን 27 ዓመታት ቢያልፈውም፤ በጣም የሚያሳዝነው ግን ባሁኑ ስዓት ይህ ከንቱ ፕሮፖጋንዳ፣ የፖለቲካ ሰው ነን በሚሉ ግለሰቦች ሳይቀር መነሳቱ ነው።

በሁለቱ ድርጅቶች መሃል የነበረው ልዩነት ግን የእናቸንፋለንና እናሸንፋለን አልነበረም። ልዩነቱ የቃላት ጫወታ አልነበረም፤ መሰረታዊ በሆኑ የአቋም፣ የፖሊሲና በአብዮቱ አካሄድ ላይ በነበራቸው ልዩነቶች ላይ የተመረኮዘ እንጂ። ይህን ለማሳየት የነበሩትን ልዩነቶች አንድ በአንድ እንመልከታቸው።

- 
- ልዩነቱ መሰረታዊ በሆኑ ዓበይት ጥይቄዎች ላይ የሚያጠነጥን ነው። ገና ከመነሻው፣ ወደ ድርጅት ከማደጋቸው በፊት፣ በተማሪ ማኅበር ትግል ውስጥ እያሉ፣ ድርጅቱን የመሰረቱትና በኋላም አባል የሆኑትን ጨምሮ በመሃላቸው የነበሩ ልዩነቶች የሚከተሉት ናቸው።
    - በአብዮትና ትግል ጥያቄ ላይ
        - በኢሕአፓ በኩል በዚያን ወቅት (በ 60 ወቹ) ኢትዮጵያ ውስጥ አብዮት (ትጥቅ ትግል) ለማካሄድ ስነልቦናዊና ተጨባጭ ሁኔታው የተሟላ ነው ሲ

        - 
        - በመኢሶን በኩል ግን የዳበረ የላብ አደር መደብ ስለሌለ አገሪቱ ለአብዮት ዝግጁ አይደለችም ይሉ ነበር።
        - በኢሕአፓ በኩል ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰብ አገር ነች፣ ስለሆነም የሚነሱት የብሔር ጥያቄዎች ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ ሊፈለግለት ይገባል ሲል
        - መኢሶኖች ግን በኢትዮጵያ ብሔሮች ሳይሆን ሪጅኖች ነው ያሉት ይሉ ስለነበር ይኸው አሁን ድረስ የሚያውከንን የብሔር ጥያቄን አልተገነዘቡም፣ ስላልተገነዘቡትም መፍትሔ አይሹም ነበር
- በፖለቲካ ድርጅት ደረጃ ከተደራጁና የየካቲት ሕዝባዊ አብዮት ከፈነዳ በኋላም ልዩነታቸው በርከት ባሉ መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተንጸባረቁ። ልዩነቶችን ከዚህ በታች አንድ ባንድ እናያቸዋለን።
    - በደርግ ባህሪ ላይ የተስተዋለው ልዩነት
        - በኢሕአፓ በኩል ደርግ ጸረ ዴሞክራሲ፣ ጸረ ሕዝብ የሆነ ኢዴሞክራሲያዊ ወታደራዊ መንግሥት ነው። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተሳትፎበት የተካሄደውን ሕዝባዊ ዓመጽ የነጠቀ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ነው ይላል
        - ደርግ ወታደራዊ ሃይል እንደመሆኑ መጠን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓብዮቱ ያነሳቸውን መሰረታዊ ጥያቄዎች ይጻረራል፣
            - የመሬት ላራሹን ጥያቄ ይዞት ከባላባቶች ነጥቆ ወደ መንግሥት ይዞት ቀየረ እንጂ መሬት ላራሹ አላደረገም
            - መሰረታዊና ዓለም አቀፋዊ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች
                - በነጻ የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብቶችን ተጻርሮ በአዋጅ አግዷል። ከዚህም አልፎ፣ "ማሰብንም" በአዋጁ እንደ ወንጀል ፈርጆታል።
            - የብሔር ጉዳይ፣ በልዩ ሁኔታ የኤርትራን ጥያቄንም ጨምሮ፣ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፈታት አለበት የሚለውን ተጻርሯል
    - በመኢሶን በኩል የተያዘው አቋም ባንጻሩ
        - ደርግ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ነው፣ ስለዚህም ሊደገፍ ይገባዋል

- ከላይ የተጠቀሰው መሰረታዊ ነጥቡ ሲሆን ከዚህ አቋሙ የሚከተል ሌሎች ልዩነቶችም ነበሩ
    - ደርግ ጋር ሙሉ በሙሉ በመወገን የደርግን ጨቋኝ ሜካኒዝም (የቀበሌ ማኅበራት፣ ሴኩሪቲ መዋቅሮችን) ከነሶቪየት ኅብረትና ምስራቅ ጀርመን ጋር በማበር አደራጅተየዋል።
    - በዚያን ወቅት አሰሳ፣ ነጻ እርምጃና ቀይ ሽብር የሚባሉ ኢሰብአዊና ኢዴሞክራሲያዊ አካሄዶችን በመፍጠር (ራሳቸው በፈጠሩት መሳሪያ ከመበላታቸው በፊት) ሙሉ ትውልድ አምክነዋል
    - በንጉሡ ጊዜ፣ ሙሉ በሙሉ ነጻና የተሟሉ ባይሆኑም፣ ተደራጅተው የነበሩ ሕዝባዊ ማኅበራት (የሰራተኛ፣ የተማሪዎች) በማውደም በምስላቸው ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሯቸው አስመሳይ ድርጅቶች በመፍጠር ወደ ጭቆና መሳሪያነት ቀይረዋቸዋል።

- በብሔር ጥያቄ ላይ
    - ኢሕአፓ ደርግ ብሔሮችን በሚመለከት ይከተለው የነበረውን የደምስሰው፣ አጥፋው አምክነው ፖሊሲ ገና ከመጀመሪያው ይቃወመው ነበር። እንደ መፍትሔ የያዘው አቋም ችግሩ ሊፈታ የሚችለው ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ነው ብሎ ሲያምን
    - በመኤሶን በኩል ግን የደርግ ተቀጥላ በመሆን በያካባቢው ይነሱ የነበሩትን የብሔር ጥያቄዎች ሊፍቱ የሞከሩት በመሳሪያ ኃይል ነበር። በግልጽ አይተነዋል አልሰራም። የደርግና የመኢሶን አካሄድ ለጠባብ በሔርተኞችና ተገንጣይ ኃይሎች ምቹ ሁኔታን ፈጥሮ ኢትዮጵያ በቁጥጥራቸው ስር እንድትወድቅ አደረገ እንጂ።

ልዩነቱ ከላይ የተዘረዘረው ነበር - የእናቸንፋለን/እናሸንፋለን አልነበረም። ለዚህም ነው አንዳንድ ኃይሎችና ግለሰቦች በደርግ የጎብልስ (Joseph Goebbels) ዓይነት ፕሮፖጋንዳ አሁን ድረስ መዳከር የሚያስተዛዝበውና የሚያሳዝነው።